የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17[th] Year No. 55
ADDIS ABABA 19[th] May 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፵፪/፪ሺ፫

ለክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ ፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ...ገጽ ፭ሺ፰፻፶፪

## CONTENTS

Regulation No. 242/2011

Federal Board Providing Affirmative Support for Regions Establishment Council of Ministers Regulation....Page 5852

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፪/፪ሺ፫

## ለክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ ፌዴራል ቦርድ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ለክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ ፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፪/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ክልሎች" ማለት የአፋር ክልል፣ የሶማሌ ክልል፣ የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል እና የቤኒሻንጉል/ጉሙዝ ክልል ናቸው፤

፪/ "ልዩ ድጋፍ" ማለት በዋነኛነት ክልሎችን በወሳኝ የልማትና መልካም አስተዳደር መስኮች አቅማቸውን በሚገነባ መንገድ ልዩ እገዛ በመስጠት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ የሚደረግ እገዛ ነው፡፡

**፫. መቋቋም**

፩/ ለክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ ፌዴራል ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 242/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF FEDERAL BOARD PROVIDING AFFIRMATIVE SUPPORT FOR REGIONS.

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Federal Board Providing Affirmative Support for Regions Establishment Council of Ministers Regulation No. 242/2011".

**2. Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "regions" means the State of Afar, the State of Somali, the State of Gambela Peoples and the State of Benshangul/Gumuz;

2/ "affirmative support" means support provided to regions mainly in a manner of capacity building in the decisive areas such as economic development and good governance to ensure their rapid and sustainable growth.

**3. Establishment**

1/ The Federal Board Providing Affirmative Support for Regions (hereinafter the "Board") is hereby established.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.10

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፪/ የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

፬. <u>የቦርዱ አባላት</u>

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም ኃላፊ ............ ሰብሳቢ

፪/ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ...... ምክትል ሰብሳቢ

፫/ የግብርና ሚኒስትር .................... አባል

፬/ የትምህርት ሚኒስትር................ አባል

፭/ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር .................አባል

፮/ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ........... አባል

፯/ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ..............አባል

፰/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች ኃላፊዎች ..........................አባላት

፭. <u>ዓላማ</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ የፌዴራል መንግስት አካላት ለክልሎች የሚሰጡትን ልዩ ድጋፍ የማስተባበር፣ የመምራትና ውጤታማነቱን የማረጋገጥ፤

፪/ ክልሎቹ ቀጣይ የልማት ማስፈጸም አቅም ለመገንባትና በመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ላይ ለሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ፤

፫/ ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎችና በአጎራባች ክልሎች መካከል የትብብር ግንኙነት እንዲጠናከር የማበረታታት፡፡

፮. <u>የቦርዱ ኃላፊነትና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ክልሎች ራሳቸውን እንዲችሉ ቀጣይነት ያለው የማስፈጸም አቅም ግንባታ ዕገዛ ያደርጋል፤

፪/ በክልሎቹ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል የዕቅድ ሐሳብ ያመነጫል፤ በዕቅድ አዘገጃጀት፣ አፈጻጸምና ክትትል የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

፫/ በልማትና በመልካም አስተዳደር ለክልሎቹ የሚደረገውን የፌዴራል ልዩ ድጋፍ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ውጤታማነቱንም ያረጋግጣል፤

2/ The Board shall be accountable to the Prime Minster.

4. **<u>Members of the Board</u>**

The Board shall have the following members:

1/ an official to be designated by the Prime Minster.................................Chairperson

2/ the Minister of Federal Affairs............... ...................... ........Deputy Chairperson

3/ the Minister of Agriculture.... Member

4/ the Minister of Education............Member

5/ the Minister of Health..............Member

6/ the Minister of Water and Energy... Member

7/ the Minister of Civil Service........Member

8/ other officials to be designated by the Prime Minster ..............................Members

5. **<u>Objective</u>**

The objectives of the Board shall be to:

1/ direct, coordinate and ensure the effectiveness of affirmative support provided by organs of the Federal Government for regions;

2/ provide the necessary assistance for regions in their effort to build their implementation capacity for sustainable development and in promoting good governance and democratization;

3/ encourage close cooperation between the regions eligible for affirmative support and neighboring regions.

6. **<u>Responsibilities and Duties of the Board</u>**

The Board shall have the responsibilities and duties to:

1/ provide sustainable implementation capacity building support for regions to make them self-reliant;

2/ initiate planning ideas to ensure rapid and sustainable growth of the regions; provide them with integrated support in respect of plan preparation, implementation and follow up;

3/ direct and coordinate the federal affirmative support provided for regions with respect to development and good governance, and ensure its effectiveness;

፬/ ለክልሎቹ የሚደረገውን የፌዴራል ልዩ ድጋፍና የአጎራባች ክልሎችን ትብብር ያቀናጃል፤

፭/ ተገቢ ሙያና ልምድ ያላቸው አባላት የሚገኙበት የፌዴራል የልዩ ድጋፍ የቴክኒክ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

፮/ ዓላማውን በብቃት ለማሳካት መገኘት አለባቸው ብሎ ያመነባቸውን አካላት በቦርዱ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ያደርጋል።

**፯. የቦርዱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢ የቦርዱን ስራዎች በበላይነት ይመራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርዱ ሰብሳቢ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ እና ፲ የተመለከቱትን ኃላፊነትና ተግባራት በስራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) የቦርዱን ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል።

**፰. የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**

የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ፦

፩/ የቦርዱ ሰብሳቢ በሌለበት ወቅት ተክቶ ይሰራል፤

፪/ የልዩ ድጋፍ የቴክኒክ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፤

፫/ የቦርዱ አባላት የወልና የተናጠል ኃላፊነትና ተግባሮቻቸውን በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል።

**፱. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ኃላፊነትና ተግባር**

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፦

፩/ የቦርዱና የልዩ ድጋፍ የቴክኒክ ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

፪/ የፌዴራል ድጋፉን የሚያቀናጅ ማዕከል በመሆን የቦርዱን ውሳኔዎች አፈጻጸም ይከታተላል፤

፫/ የልዩ ድጋፉን አፈጻጸም በሚመለከት በየሩብ ዓመቱ ለቦርዱና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ያቀርባል።

4/ coordinate the federal affirmative support provided for the regions and the cooperation of neighboring regions;

5/ establish federal affirmative support technical committee composed of members having the required profession and experience;

6/ call relevant bodies to attend its meetings where it believes that their participation is indispensable for the successful achievement of its objectives.

**7. Powers and Duties of the Chairperson**

1/ The Chairperson shall direct the activities of the Board.

2/ Without prejudice to the generality of sub-article (1) of this Article the Chairperson shall:

a) ensure that the responsibilities and duties stated under Articles 6 and 10 of this Regulation are discharged;

b) call and preside over the meetings of the Board.

**8. Powers and Duties of the Deputy Chairperson**

The Deputy Chairperson of the Board shall:

1/ act on behalf of the Chairperson in the absence of the latter;

2/ preside over the meetings of the Affirmative Support Technical Committee;

3/ follow up and coordinate the proper execution of common and individual responsibilities and duties of Board members.

**9. Responsibilities and Duties of the Ministry of Federal Affairs**

The Ministry of Federal Affairs shall:

1/ serve as the Secretariat of the Board and the Affirmative Support Technical Committee;

2/ serve as a coordinating center of federal affirmative support and follow up the implementation of decisions of the Board;

3/ submit quarterly reports to the Board and the Prime Minister.

**፲. በቦርዱ አባላት የሚመሩ መስሪያ ቤቶች ኃላፊነትና ተግባር**

በቦርዱ አባል የሚመራ ማንኛውም መሥሪያ ቤት በማቋቋሚያ ሕጉና በሌሎች ሕጎች የተሰጡት ኃላፊነትና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ ለክልሎች የሚሰጠውን ልዩ ድጋፍ በሚመለከት የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ከክልሎቹና ከአጎራባች ክልል አቻ ሴክተር ቢሮዎች ጋር በመሆን ዘላቂ ልማትና እድገት ሊያመጡ የሚችሉ ወሳኝ የልማትና የአቅም ግንባታ ጉዳዮችን በመለየት ያቅዳል፣ ከሀገራዊ ግቦችና ስታንዳርዶች አኳያ የተጣጣሙ እንዲሆኑ በማድረግ ይተገብራል፣ ይገመግማል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

፪/ በጋራ የተያዙ የወሳኝ ጉዳዮች ዕቅድ በተገቢው መንገድ ለማሳካት የሚያስችል የራሱን የልዩ ድጋፍ አደረጃጀት ይፈጥራል፤ እንደአስፈላጊነቱ ብቁ የሰው ኃይል በየክልሉ በማሰማራት ዕቅዱ ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፤

፫/ የዕቅድ አፈጻጸሙን ተግባራዊ ለማድረግ በየክልሎቹ እና በየደረጃው በሚገኘው አቻ አደረጃጀት አቅም ከማሳደግ አኳያ በሰው ኃይል ስልጠና፣ በአደረጃጀትና በአሰራር ስርዓቶች የአቅም ግንባታ ስራ በተገቢው መንገድ ይተገብራል፤

፬/ ለዕቅድ አፈጻጸም ጠቃሚ የሆኑ የሀገር ውስጥና የውጪ ልምዶች እንደየ ክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ ተቃኝቶ እንዲካተትና እንዲተገበር ያደርጋል፤ በክልሎቹ መካከልም በሴክተሩ የተሻለ ልምዶች ልውውጥ በማድረግ እንዲ ስፋፋ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፭/ በክልሎቹ ሊሸፈኑ የማይችሉ ግብዓቶችን በመለየት ያቀርባል፤ አፈጻጸሙን በቅርበት በመከታተል ይደግፋል፤

፮/ በየሩብ ዓመቱ የዕቅድ አፈጻጸምን ከክልሎቹና ከአጎራባች ክልሎች አቻ የሴክተር አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር በመሆን ይገመግማል፤ በተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች አማካይነት ለቦርዱ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ያቀርባል።

**10. Responsibilities and Duties of Institutions Headed by Members of the Board**

Without prejudice to the responsibilities and duties given to it by its establishment legislation and other laws, every institution headed by a member of the Board shall have the following duties and responsibilities with regard to affirmative support to be provided for regions:

1/ in collaboration with the regions and parallel sectoral neighboring regional bureaus, identify and plan development and capacity building issues decisive to sustainable development and growth and, upon ensuring their compatibility with the country's objectives and standards, implement, evaluate and ensure the effectiveness of same;

2/ create its own affirmative support structure to successfully implement jointly prepared plans of decisive issues and, if necessary, deploy competent human power in the regions to make the plan effective;

3/ undertake proper capacity building measures with respect to human power training, organizing and system development at the levels of the regions and parallel structures to realize implementations of the plans;

4/ ensure, by taking into account the objective conditions of the regions, the incorporation and implementation of relevant local and foreign best practices in the implementation of plans, and create conducive conditions for the scale up of same through exchange of sectoral experiences among the regions;

5/ identify and provide inputs that could not be availed by the regions themselves; and closely follow up and support the execution of same;

6/ undertake quarterly plan implementation evaluations together with parallel sectoral leaders and professionals of neighboring regions, and present plan implementation reports to the Board through its top officials.

**፲፩. የቦርዱ ስብሰባዎች**

፩/ ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሐሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፪. ስለክትትልና ግምገማ**

፩/ በቦርዱ አባላት የሚመሩ መስሪያ ቤቶች ከፍተኛ ኃላፊዎች በአንደኛውና በሶስተኛው ሩብ ዓመት በየክልሉ በመገኘት የክልሉ ከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች በተገኙበት የእቅድ አፈጻጸም ይገመግማሉ፤ በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ወሳኝ ጉዳዮችን በጋራ ይለያሉ፣ ማካካሻ እቅድ ያፀድቃሉ፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላሉ፡፡

፪/ የቦርዱ አባላትና የየክልሉ የበላይ አመራሮች በሁለተኛውና በአራተኛው ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም በጋራ ይገመግማሉ፣ ቀጣይ የልዩ እገዛ እቅድ አቅጣጫ ያፀድቃሉ፡፡

**፲፫. ተጠያቂነት**

በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ያልተወጣ የፌዴራል መሥሪያ ቤት አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፲፬. የተሻረ ደንብ**

በልማት ወደኋላ ለቀሩ ክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ የፌዴራል ቦርድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፫/፲፱፻፺፮ (በደንብ ቁጥር ፩፻፳፰/፲፱፻፺፱ እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፲፭. መመሪያ ስለማውጣት**

ቦርዱ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**11. Meetings of the Board**

1/ The Board shall meet once every three month; provided, however, that the Chairperson may call extraordinary meeting when necessary.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at a meeting.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority vote, in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article the Board may adopt its own rule of procedure.

**12. Monitoring and Evaluation**

1/ Senior officials of institutions headed by members of the Board shall, by being present in every region and jointly with senior regional officials and professionals, evaluate implementation of plans at the end of the first and third quarters and thereby identify critical issues, adopt contingency plans and follow up their implementation.

2/ Members of the Board and the top leadership of the regions shall jointly evaluate implementation of plans at the end of the second and fourth quarters and approve directions for the preparation of subsequent plans.

**13. Accountability**

Any federal institution failing to discharge its responsibilities and duties provided for under this Regulation shall be held liable in accordance with relevant laws.

**14. Repealed Regulation**

The Federal Board to Provide Affirmative Support for Less Developed Regions Council of Ministers Regulation No.103/2004 (as amended by Regulation No. 128/2006) is hereby repealed.

**15. Power to Issue Directives**

The Board may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

፲፮. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከመጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

16. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the 1st day of April, 2011.

Done at Addis Ababa, this 19th day of May, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት